# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ጥቅምት 25/2000

**መግለጫ**

**የሚዘጋጀው ጦርነት የሕዝብ እልቂት እንጂ የሚያመጣው አንዳችም ጥቅም አይኖርም**

ሰሞኑን የሚደርሱን ዜናዎችና በዓለም ዙሪያ የሚገኙ የመገናኛ ብዙኃን፥ በዓይነታ ወሪያቸው ላይ በወያኔና በሻአቢያ መካከል ከፍተኛ የጦርነት መሰናዶ እንዳለ በሰፊው ይተነትናሉ፡፡ ለዚህ ጦርነት ዝግጅት ይረዳ ዘንድም ከየአቅጣጫው መጠነ ሰፊ የሆነ ከባድና ቀላል የጦር መሳሪያ ወደ ድንበር ከሁለቱም በኩል በመጉረፍ ላይ እንደሆነ በርካታ የዓይን ምስክሮች ስጋታቸውን በመግለፅ ላይ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ከማንም በበለጠ ያስጨነቃቸው የኢትዮጵያና የኤርትራ ወገኖቻችን እንደሆኑ ማንም የሚያምነው ነው፡፡ ማነኛውም ጦርነት የሚያስከትለውን ጉዳትና ከዚህ በፊትም በዚሁ አካባቢ ከ መቶ ሺ በላይ ህይወት መጥፋቱን የሚያውቀው ዜጋ ሁሉ በአካባቢው የሚያንዣብበውን የጦርነት መርዶ በሀዘን ከመመልከት ባሻገር፥ በቸልታ የሚያልፈው አይሆንም፡፡

የአካባቢያችን ነዋሪዎች ከማንምና ከምንም በላይ የሚፈልጉት ሰላምና መረጋጋት እንጅ፥ ዕልቂትና ፍጅትን የሚያስከትል የጦርነት ውድመት እንዳልሆነ፥ ከእነርሱ በበለጠ ሌላ የሚያውቀው የለም፡፡ በዓለም ሕዝቦች ዘንድ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ በድህነት፥ በበሽታና በጉስቁልና የሚኖሩ መሆናቸው የዓለም አቀፍ የጥናትና የምርምር ማዕከሎች በማስረጃ የተደገፈ ዘገባ ያቀርባሉና ዛሬ ኤርትራና ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋቸው፥ የእህል ጎተራ፥ የአዝመራ አውድማ እንጅ፥ የሬሳ ክምርና የቁስለኞች ቁልል አይደለም፡፡ መለስና ኢሳያስ ከጥቂት ዓመታት በፊት በካሄዱት ትርጉም የለሽ አውዳሚ ጦርነት፥ ጎልቁ ማሳፍረት ሰላማዊ ዜጎች በሁሉቱም ወገን ህይወታቸውን አጥተዋል፥ ዕልፍ አዕላፉም ቆስለዋል፡፡ በቢሊዮን የሚቆጠር ሀብት- ንብረት ወድሟል፡፡ በአያሌ ሽህ የሚቆጠሩ ህፃናት ያለ አሳዳጊ ቀርተዋል፡፡ አረጋውያን አባቶችና እናቶች ያለ ጧሪ ወድቀዋል፡፡ አቋጣሪ በማጣትም ተረስተዋል፡፡ ይህ ሁሉ ጥፋትና ውድመት ሆኖ አንዳችም ውጤት አልተገኘም፡፡ ዋይታና ሀዘኑ ግን አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡ የሰላምና የመረጋጋት ተስፋም የፆም ውሃ ሆኖ ቀርቷል፡፡ የተጠቀሙ ቢኖሩ፥ የዓለም ጦር መሳሪያ ፋብሪካዎችና የጦር መሳሪያ ነጋዴዎች ብቻ ናቸው፡፡ የሕዝባችን ደምና አፅም የባዕዳን መበልፀጊያ ሆኖ እስከመቸ እንደሚቀጥል ግን የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን፥ የሚያስገርምም ክስተት ሆኖብናል፡፡

አምባገነን ሥርዓቶች በየጊዜው የሚጭሩት ጦርነት መቸ መቆም እንዳለበት፥ ማንስ ለማቆም እንደሚችል በትክክል ለመናገር የሚችል የለም፡፡ የውስጥ ችግራቸውን ለመሸፈንና የሕዝብን ዕይታ ወደ ሌላ ለመጎተት ጦርነት መጫር፥ የጨቋኝ ገዢዎች ልምድ ነው፡፡ ሀገራችን የቅርብ ጎረቤትም ይሁን የሩቅ ዘመድ እንደሌላት ይህ ያለፈው የሠላሳ ዓመታት የሰቆቃ ጊዜ ቁልጭ አድርጎ አሳይቶናል፡፡ አምባገነኖች በውስጥ ያለውን ሕዝባዊ አመፅና ትግል አቅጣጫ ለመለወጥና ትኩረትም ለማወናበድ ሲሉ የሚያደርጉት ይህ የጦርነት መሰናዶ በማያወላውል መልኩ ሁሉም ዜጋ ሊቃወመውና ሊያከሽፈው ይገባል፡፡ ሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች፥ አምባገነኖች በሚጭሩት ጦርነት መማገድና ማለቅ የለባቸውም ብሎ ኢሕአፓ ያምናል፡፡ የመለስ አገዛዝ ሶማሊያ ውስጥ እያካሄደ ያለው ጦርነትና አሁንም በሰሜን ሊጭረው የተነሳው ጦርነት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልጋቸው ጦርነቶች አይደሉም፡፡ የሚጠቅሙት ለባዕዳንና ለወያኔ አገዛዝ ብቻ ስለሆነ፥ ኢሕአፓ ጦርነቱን

ከወዲሁ አጥብቆ ይቃወማል፡፡  ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ ጦርነቱን እንዲያወግዝ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀዳሚና ዋና ተግባር ወይም ትግል የወያኔን አገዛዝ ማስወገድ ነው፡፡**

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**


**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes
92270
France

**E-mail** **ESPIC@aol.com**   **Website:** **http://www.EPRP.com**